# ከሕግ ፋኩልቲ የተሰጠ የ፲፱፻፸፩ እና የ፲፱፻፸፪ ዓ/ም

## ራፖር ።

ፋሲል ናሆም ፣ ዲን

የሕግ ፋኩልቲ በዚህ የኅብረተሰብአዊ ለውጥ የተጧጧፈባት ወሳኝ አብዮታዊ ወቅት ብሔራዊ ፍላጎትትን እንዲያሟላ ለማድረግ የተወጠነው ታላቅ ተግባር ከመቸውም ይበልጥ የተሰማበት ጊዜ ነው ። ይህንንም የምንልበት ምክንያት ከፊታችን የተደቀነውን አስቸጋሪው ተግባር ለመቋቋም ወደፊት የሚመጣው ጊዜ ከአለፈው የተሻለ የሥራ ውጤቶች ይኖሩታል የሚል ጽኑ እምነት ስላለን ነው ። የሕግ ፋኩልቲ በ፲፱፻፶፮ ዓ/ም መቋቋምና የኢትዮጵያ ሕጐች በመጽሐፍ (በኮድ) መውጣታቸው ወዲያውኑም ተከታትለው የመጡት አስር ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ በሕግ መስክ ተገቢ ለሆነ ትምህርትና ምርምር መሠረት ጥለዋል ። ምንም እንኳን በጊዜው በምሁራን አካባቢ የነበረው ሁኔታ ለመቅዳት ፣ ለማስተጋባትና ከቀድሞው ትምህርታዊ ወግ እልፍ እንዳይሄድ የታቀደ ለጥቂት ምርጥ ሊቃውንት ብቻ የተዘጋጀና ቀለም የለሽ ፖለቲካ ሰፍኖበት የነበረ ሁኔታ ቢሆንም ፣ የሕግ ፋኩልቲ በኢትዮጵያ መሬት ላይ መቋቋምና ኢትዮጵያዊ ችግሮችን መመርመሩ በእርግጥ ከፍተኛ እድገት ነበር ማለት ይቻላል ። ሆኖም ብዛት ያላቸው የውጭ አገር መምህራን ወደአገራቸው በመመለሳቸውና ያሉትም ጥቂት ወጣት ኢትዮጵያውያን መምህራን ለከፍተኛ ትምህርት ወደውጭ በመሄዳቸውም ሆነ በከፍተኛ የመንግሥት ሥራዎች ላይ በመሳተፋቸው የሕግ ፋኩልቲው የተመኘውን ያህል በሙሉ ጉልበትና በከፍተኛ ደረጃ ሊያመርት አልቻለም ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ የሕግ ፋኩልቲ ከአለበት ከፍተኛ የመምህራን እጥረት ገና ማገገም አለበት ፤ ከዛሬው ከጥቂት የመምህራን ቁጥር እልፍ በሚያስተማምን አኳኋን ሥራውን ማከናወን ይኖርበታል ። እነዚህን የትምህርት ዘመናት የጀመርነው መላውን የሕግ ፋኩልቲ ለማንቀሳቀስ ስድስት የሙሉ ቀን መምህራን እና አንድ የግማሽ ቀን መምህር ብቻ በመያዝ ነው ። በሌላው በኩል ፋኩልቲው በታሪኩ ውስጥ በነዚህ ሁለት ዓመታት ካለው የበለጠ የተማሪዎች ብዛት አጋጥሞት አያውቅም ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሚቻለው ሁሉ ለተማሪው ጥሩ የሕግ ትምህርት ለመስጠት ታቅደው የተደረጉት የሥርዓተ ትምህርት ለውጦች እነዚህን ዓመታት አጣዳፊና አስጨናቂ አድርገዋቸዋል ። ቢሆንም ወደፊት መጓዝ የሚቻለው በትግል ነውና ካከናወናቸው የሥራ ውጤቶች አንፃር ሲታይ ፋኩልቲው ላካሄደው ትግል በበቂ አኳኋን ተከሶአል ለማለት እንችላለን ። ጎላ ብለው ከሚታዩት የሥራ ውጤቶች አንዳንዶቹን ከዚህ እንደሚከተለው መጥቀስ እንወዳለን ።

፩ኛ/ <u>የሥርዓተ ትምህርት ዕድገት</u>

ሀ/ <u>ስለሥርዓተ ትምህርት ጥናት የተደረገ ስብሰባ ፣</u> በመንግሥት አስተዳደር የፖሊሲ አውጭ አካል ተሳታፊ በመሆን የሚያገለግል ፣ በሙያው ችሎታ ያለውና በፖለቲካ የታነጸ ምሩቅ ለማውጣት ለአያሌ ዓመታት በፋኩልቲው ሥርዓተ ትምህርት ላይ ሰፊ ሙከራ ሲደረግ ከቆየ በኋላ ስለሥርዓተ ትምህርት ጥናት ስብሰባ ተዘጋጀ ። ስብሰባው መምህራን ፣ ምሩቃንና የመንግሥት ባለሥልጣኖች የተሳተፉበት ከሐምሌ ፯ እስከ ፰ ፲፱፻፸፩ ዓ/ም የተካሄደ የሦስት ተከታታይ ቀናት ሥራ ነበር ። የሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ተቀዳሚ የሰው ኃይል ፈላጊና ለፋኩልቲውም መጠናከር አሳቢ አካል እንደመሆኑ ፣ በቋሚ ተጠሪው በሚመራ አራት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች በሚገኙበት ቡድን ተወክሎ በስብሰባው ላይ ተገኝቶ ነበር ። በአብዛኞቹ ሚኒስቴሮችና የመንግሥት ድርጅቶች የሚገኙ ዋና የሕግ አማካሪዎችና እንደዚሁም የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኞችና የቀበሌ ማኅበራት የፍርድ ሸንጎ አባላት በስብሰባው ተካፍለው ነበር ። በተጨማሪም የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ተወካይና የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት በሕግ ባለሙያነታቸውና በሥራቸው ምክንያት በስብሰባው ላይ ተካፍለው ነበር ።

ስብሰባው በነበረው ሥርዓተ ትምህርት ላይ በሰፊው ተንጋግሮ ጥልቀት ያላቸው ማሻሻያዎችና የፖሊሲ ውሳኔዎች ለመቅረጽ በመቻሉ የተሳካ ስብሰባ እንደነበር እዚህ ላይ ማስታወስ እወዳለሁ ። በእርግጥ እነዚህ ጠቃሚ ማሳሰቢያዎችና ማሻሻያዎች የሚያመለክቷቸው ሁኔታዎችና አፈጻጸማቸው በፋኩልቲው በጥንቃቄ የሚታዩና የሚቀናጁ የረጅም ጊዜ እቅዶች ናቸው ። (በእንግሊዝኛ ተጨማሪ ፩ና ተጨማሪ ፪ የተባሉትን ጽሑፎች ይመልከቱ ።)

ለ/ <u>ሥርዓተ ትምህርት</u> ፣ የሥርዓተ ትምህርቱ ስብሰባ ባቀረበው ሐሳብና በፋኩልቲውም በተካሄዱት ውይይቶች ላይ የተመሠረተ ከ፲፱፻፸፪ ዓ/ም የትምህርት ዘመን ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለው አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ተዘጋጅቶአል ። በእርግጥ

የሥርዓተ ትምህርት መሻሻል የማያቋርጥ ሂደት
ነው ። ሥርዓተ ትምህርቱ በየጊዜው እንደገና
እንዲታይና ወቅታዊ መልክ እንዲኖረው ማድረግ
ያስፈልጋል ።

## ፪ኛ/ ምርምር ማድረግና ጽሑፎችን ማውጣት ፤

ምርምር የማድረግና ጽሑፎችን የማውጣት
ሥራ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ለማስተማር በጣም
አስፈላጊ ነገሮች መሆናቸውን ፋኩልቲው ከረ
ጅም ጊዜ ጀምሮ ተገንዝቧል ። እንደሕግ ፋኩ
ልቲ በመሰለ የሙያ ትምህርት ቤት ምርምር
ማድረግና የምርምር ውጤት የሆኑ ጽሑፎችን
ማውጣት እንዲያውም የበለጠ ተፈላጊነት ይኖራ
ቸዋል ። ምንም እንኳን ያለው ከፍተኛ የመምህ
ራን እጥረት ባለፉት አያሌ ዓመታት ውስጥ ምር
ምር የማድረግንና ጽሑፎችን የማውጣትን ሥራ
አዳጋች አድርጎት የነበረ ቢሆንም ፤ ፋኩልቲው
በአሁኑ ሰዓት በእነዚህ አካባቢም ድፍረት ያለው
እርምጃ መደረግ እንዳለበት ወስኗል ።

ሀ/ የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ፤ ከዚህ በላይ በተጠ
ቀሰው ዓላማ ፋኩልቲው የኢትዮጵያ የሕግ መጽ
ሔት እንደገና እንዲያንሰራራ አድርጓል ። የአዘ
ጋጆዎች ቡድን ተሰይሟል ። የሕግ አዋቂዎች
ጽሑፎችና አስተያየቶች ተጠይቀዋል ፤ የአዘጋጂ
ዎች ቦርድም ተቋቁሟል መጽሔቱ አግባብ
ላለው የሕግ ምርምር መድረክ ብቻ ሳይሆን ፤
በአገሪቱ ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሕግ
ሙያ የተሰማሩ ሊቃውንት የሚገናኙበት ማዕከላዊ
ዘዴም በመሆኑ ተፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው እንላለን ።
ከዚህም በላይ ይህ መጽሔት የአብዮታዊት ኢትዮ
ጵያን ህብረተሰብአዊ እርምጃዎች በትክክል የሚ
ያንጸባርቅ እንዲሆንና ጠለቅ ያሉ አከራካሪ የሕግ
ጭብጦችን የሚፈታና ከፍተኛ የሕግ ዕውቀት የሚ
ያሰራጭ መሆን ይኖርበታል ። ስለዚህም የመጽ
ሔቱ አዘጋጆች ቦርድ አባላት ከሕግ ምሁራን ፤
ከፍተኛ ዳኞችና የመንግሥት ባለሥልጣኖች ተመ
ርጠው እንዲገቡበት ተደርጓል ። የዚህም መላው
የሕግ ባለሙያዎች ቡድን ቅንብር የተደረገው
ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው የሕግ አዋቂዎችናን የፖ
ለቲካ ብስለት ያላቸው ግለሰቦችን በመሰብሰብ
የመጽሔቱን ጥራት ለማረጋገጥ ታስቦ ነው ። ይህ
ራፖር ወይም መግለጫ በሚጻፍበት ጊዜ የመጽ
ሔቱ የመጀመሪያው ክፍል ወደ ማተሚያ ቤት
በመላክ ላይ ነው ። እዚህ ላይ የዩኒቨርሲቲ አስ
ተዳደር በመጽሔቱ ማንሰራራት ላሳየው የጋለ
ድጋፍና ማበረታቻ የፋኩልቲውን ምስጋና መጥ
ቀስ ይገባኛል ።

ለ/ የኢትዮጵያ የተጠቃለሉ ሕጎች ፤ ሌላው ፋኩልቲው
እንዲያንሰራራ የወሰነው ምርምር የማድረግና
ጽሑፍ የማውጣት ሥራ የተጠቃለሉ የኢትዮጵያ
ሕጎችን ነው ። የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜ
ያዊ ወታደራዊ መንግሥት ያወጣቸው አዳዲስ ሕጎች
ገና መጠቃለል ይኖርባቸዋል ። ሥራው ለብዙ
የመንግሥትና የሕዝብ ተቋሞች እጅግ አስፈላጊ
ነው ። ለዚህም እጅግ ጠቃሚ ሥራ ችሎታ ያላቸው
አዘጋጂዎች ተመርጠው ሥራውን በማካሄድ ላይ
ይገኛሉ ።

ሐ/ የፋኩልቲና የግል ምርምር ፤ የፋኩልቲው አባላት
ከማስተማር ፣ ፋኩልቲ አቀፍና ዩኒቨርስቲ አቀፍ
በሆኑ የአስተዳደር ሥራዎች ውስጥ ከመሳተፉ
በላይ በተጨማሪ ፤ የፋኩልቲና የግል ምርምር
ውጥኖች በማካሄድ የመጀመሪያ ፍሬአቸው የሆ
ነውን ይህን የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት እትም
ለማውጣት በቅቷል ።

## ፫ኛ/ የውጭ ግንኙነቶች ፤

የትኛውም ፋኩልቲ ቢሆን ራሱን የቻለ ለብቻ
ው የቆመ ደሴት አይደለም ። በተለይም በሙያ
ትምህርት ቤት ውስጥ ከፋኩልቲው ውጭ ካሉ
ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ያለማቋረጥ ግንኙነት
የማድረጉ አስፈላጊነት ምንም የማያጠያይቅ ጉዳይ
ነው ። የሕግ ፋኩልቲ በነዚህ ዓመታት ከሌሎች
ድርጅቶችና የትምህርት ተቋሞች ጋር ግንኙነት
ለመፍጠር ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ሞክሯል ።

ሀ/ ዩኒቨርስቲ አቀፍ ትብብር ፤ በማስተማሩ ደረጃ ከሁ
ለት የሶሻያሊስት ዩኒቨርስቲዎች ማለትም ፣ በፖ
ላንድ ከሚገኘው ከዋርሶው ዩኒቨርስቲና በጀርመን
ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ከሚገኘው ከላይፕዚግ
ካርል ማርክስ ዩኒቨርስቲ ጋር ጥሩ ግንኙነት ጀም
ረናል ። ከዚህም ግንኙነታችን የተነሳ ፣ ከዋርሶው
የሕግና የአስተዳደር ትምህርት ቤት ሁለት ረዳት
ፕሮፌሰሮች በሁለት ዓመት ውል አስመጥተናል ።
በተጨማሪም ከካርል ማርክስ ዩኒቨርስቲ በ፲፱፻፹፩
ዓ/ም ለአምስት ሳምንታት የመጡ አንድ ፕሮፌሰር
አግኝተናል ። ጀርመናዊው ፕሮፌሰር በፋኩልቲው
ውስጥ ከሰጡት ትምህርት በተጨማሪ ቁጥራቸው
ከአንድ ሺህ አምስት መቶ በላይ ለሆኑ የዩኒቨር
ስቲው ተማሪዎች ስለሶሺያሊስት ሕገ መንግሥ
ቶች የተሟሉ ትምህርታዊ ገለጻ አድርገዋል ።
በውጭ ግንኙነት መምህራንን ፣ ተማሪዎችንና
ጽሑፎችን በመለዋወጥ ይህን የመሰለውን ትብ
ብር ይበልጥ ፍሬያማ ለማድረግ ይህ የመጀመሪያ
ሙከራ ብቻ ነው ።

ለ/ ከመንግሥት ተቋሞች ጋር ትብብር ፤ ከቀድሞ የፋ
ኩልቲው ተማሪዎችና ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች
ጋር ያለንን ግንኙነት በሚመለከት ረገድ ፤ ቀደም
ብሎ የተጠቀሰው የሥርዓተ ትምህርት ስብሰባና
የኢትዮጵያ የግል መጽሔት ዓይነተኛና ጠቃሚ
ግንኙነት ለመፍጠር አመች መሣሪያ ሆኖአል ።
ስለዚህም ነው የጠቅላይ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ
ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች ለማስተማሪያና ለምርምር
ሥራ የሚያገለግሉ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን አቀናጅ
ተው ለፋኩልቲው ለመስጠት ቃል የገቡልን ።

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚሠሩ የሕግ ባለ ሙያችም ስለፋኩልቲያችን ያላቸውን በጎ ፈቃድ በማሳየት የፋኩልቲውን የማስተማርና የምርምር ጥራት በከፍተኛ ደረጃ ለማራመድ የሚያስችል የሕግ ጽሑፍ (ማቴሪያል) ሊያቀርቡልን ቃል ገብ ተዋል ።

፬ኛ/ <u>የመምህራን ምልመላ ፤</u>

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የመምህራን እጥረት ዋንኛው ችግራችን ሆኖ ቆይቷል ። ችግሩን ለማ ቃለል እያሌ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ እን ገኛለን ። (፩) በጊዜያዊ መልክ ችግራችንን ለመ ፍታት አንዱ ፈጣን መንገድ ብቁ ከሆኑና ከፍተኛ ችሎታ ካላቸው የመንግሥት ሹማምንትና ኤክስ ፐርት መካከል ላስተማሪነት በትርፍ ሰዓት መቅ ጠር ነበር ። ሆኖም እነዚህ ሹማምንትና ኤክስፐርት በመደበኛ ኃላፊነታቸው ሥራ የሚበዛባቸው ግለ ሰቦች በመሆናቸው ይህ በእርግጥ ዘላቂ መፍትሔ ነው ለማለት አልተቻለም ። ፍጹም አስፈላጊ እስከ ሆነ ድረስ በከፊል ጊዜ መምህራን መጠቀማችንን እንቀጥላለን ። በተለይ በከፍተኛ ደረጃ ጠለቅ ያለ እውቀት በሚጠይቁ አካባቢዎች ችሎታ ያላቸው መምህራን የሌሉን ስለሆነ በከፊል ጊዜ መምህራን በመጠቀም ከችግሩ መውጫ አንዱ መንገድ ሆኖ አግኝተነዋል ። (፪) የውጭ አገር መምህራንን መቅ ጠሩ ችግሩን ለማቃለል የሚረዳ ሌላው መንገድ ነው ። የውጭ አገር የሕግ መምህራን በተለይም ከደረጁ የሶሺያሊስት አገሮችና ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች የሚመጡት መምህራን ይበልጥ ተቀባይ ነት ይኖራቸዋል ። (፫) ሆኖም የመምህራንን እጥ ረት ለመፍታት ዋናው መንገድ ብቁ የሆኑና ከፍ ተኛ ችሎታ ያላቸውን ኢትዮጵያውያን የሕግ ምሑ ራን ማፍራት ብቻ ይሆናል ። አስተማሪነት የዕ ድሜ ልክ ሥራ እንደመሆኑ ሕግም ከኅብረተሰቡ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ያለጥርጥር የተሳሰረ ነው ። ስለዚህም ነው የፋኩልቲውን የመምህራን እጥረት ለማስወገድ በመጨረሻው አማራጭ ማለት በኢትዮጵያውያን መምህራን እንድንጠቀም እነ ዚህ ሁለት ሁኔታዎች በተጨማሪነት የሚያስገ ድዱን ። ይህን መሠረት በማድረግ አንዳንድ እር ምጃዎች በመወሰድ ላይ ናቸው ። ሦስት አዲስ መምህራን ተቀጥረዋል ፤ እንዲሁም ሁለት መም ህራን በውጭ አገር ከፍተኛ ትምህርታቸውን ሲከ ታተሉ ቆይተው ተመልሰዋል ። ስለዚህ መምህ ራንን መመልመል በሚመለከት ረገድ የፋኩልቲ ውን በትክክለኛ አቅጣጫ መጓዝ ስገልጽ በሥራ መሟላትና በእፎይታ ስሜት ነው ። በእርግጥ ያሉን መምህራን ወጣትና መጠነኛ የሆነ የሥራ ልምድ ያላቸው ናቸው ። እነዚህን የበሰሉ ባለሙያ ማድረጉ ምርምርና ተጨማሪ የማሰልጠኛ ዕድሎች የሚያስፈልጉበት የረጅም ጊዜ ሂደት ነው ። እያሌ የፋኩልቲ አባላት ሶቭየት ሕብረትንና የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክን የጎበኙባቸው ባለፉት ሁለት የክረምት ወራቶችና በዚህም ክረምት ተሳ ትፈው እንደነበሩት ዓይነት የአጭር ጊዜ የክረምት ስብሰባዎች ተቀባይነት አላቸው ። ነገር ግን የመ ጨረሻውን ከፍተኛ ውጤት ማግኘት ይቻል ዘንድ በተገቢ ድርጅቶች ውስጥ ለምርምርና ለመሰል ጠን ይበልጥ ሰፋ ላለና ረዘም ላለ ጊዜ ለመጋለጥ መታቀድ ይኖርበታል ። በተጨማሪም መመለሳ ቸውን በጉጉት የምንጠባበቀው ከፍተኛ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙ እያሌ መምህራን እን ዳሉን መግለጽ ይገባኛል ።

፭ኛ/ <u>የዲግሪ ተማሪዎች ስታትስቲክስ ፤</u>

በ፲፱፻፹፩-፹፪ ዓ/ም የትምህርት ዘመናት ፋኩል ቲው ከመቼውም ጊዜ ቁጥራቸው የበዛ ተማሪዎች መዝግቦ በማስተማር ላይ ይገኛል ። የሕግን ሙያ ለሴቶች በመክፈት ቁጥራቸው በመጠኑም ቢሆን በዛ ያለ የሴት ተማሪዎችን የመቀበል ጤናማ ዝን ባሌ በተጨማሪ ተጀምሯል ። እውነቱን ለመናገር ከዚህ በፊት የነበሩት ዓመታት ሁሉ ተደምረው ከነበረው የሴት ተማሪዎች ቁጥር የሚበልጡ የሴት ተማሪዎች በነዚህ ሁለት ዓመታት ተቀብለናል ። ቢሆንም የሴት ተማሪዎች ቁጥር አሁንም ቢሆን ከአጠቃላይ አሥር በመቶ የሚበልጥ አይደለም ። በነዚህ ሁለት ዓመታት በፋኩልቲው ተመዝግበው ትምህርታቸውን የሚከታተሉት ተማሪዎች እንደ ዓመታቸው ሲከፋፈሉ እንደሚከተለው ይሆናሉ ።

| | | ፲፱፻፹፩ ዓ/ም | | ፲፱፻፹፪ዓም | |
|---|---|---|---|---|---|
| የሕግ ትምህርት ጀማሪዎች | | ፩፻ | ተማሪ | ፻፷ | ተማሪ |
| የሕግ ትምህርት | ፩ኛ ዓመት | ፹፯ | ” | ፻፯ | ” |
| ” ” | ፪ኛ ” | ፴፯ | ” | ፳ | ” |
| ” ” | ፫ኛ ” | ፳፯ | ” | ፵፫ | ” |
| ” ” | ፬ኛ ” | ፳፫ | ” | ፲፬ | ” |
| የማታ የሕግ ባችለር ዲግሪ | | ፳ | ” | ፳፪ | ” |

ከእነዚህ ውስጥ ፴ የ፬ኛ ዓመት የሕግ ተማሪዎችና ቀደምትነት ያላቸው የ፫ኛ ዓመት የሕግ ተማሪዎች በ፲፱፻፹፩ ዓ/ም በዲግሪ ሲመረቁ ፣ በ፲፱፻፹፪ ዓ/ም ደግሞ ፳፰ የ፬ኛ ዓመት የሕግ ተማሪዎች የ፫ኛ ዓመት የሕግ ተማሪዎችና የማታ የዲግሪ የሕግ ተማ ሪዎች ይመረቃሉ ።

፮ኛ/ <u>የሕግ ትምህርት ፕሮግራሞች ፤</u>

ከዚህ በፊት ፋኩልቲው በሕግ የባችለር ዲግ ሪን ፣ በሕግ ዲፕሎማና ሰርቲፊኬትን ጨምሮ በተ ለያዩ የሕግ ትምህርት ፕሮግራሞች ደረጃዎች ሙከራ አድርጓል ፤ በአሁኑ ወቅት ከሚሰጠው መደበኛ የቀን በሕግ የባችለር ዲግሪ ፕሮግራም የፋኩልቲው ተጨማሪ ፕሮግራም እንደሚከተ ለው ነው ፤

ሀ/ <u>በሕግ የዲፕሎማ ፕሮግራም ፤</u> ከብዙ የመንግሥት ድርጅቶች ጋር ምክክር ከተደረገ በኋላ በ፲፱፻፹፪

የትምህርት ዘመን በሥራ ላይ የዋለ የሁለት ዓመት የሕግ የዲፕሎማ ፕሮግራም በ፩፱ ተማሪዎች ተጀምሯል ። የማስተማሪያው ቋንቋ አማርኛ የሆነው ይህ ፕሮግራም በመንግሥት ድርጅቶች ውስጥ የሚያገለግሉ መለስተኛ የሕግ ባለሙያዎችን ጥራት ለመጨመር በማሰብ የታቀደ ነው ። ፕሮግራሙ ለጊዜው በአዲስ አበባ ብቻ ቢሰጥም ፤ ሁኔታዎች እስከፈቀዱ ድረስ በሌሎች ስፍራዎች ወደፊት ሊሰጥ የማይችልበት ምንም ምክንያት አይኖርም ።

ለ/ ሌሎች ፕሮግራሞች ፤ ፋኩልቲው በበቂ ሁኔታ ተሟልቶ የማታውን በሕግ የባችለር ዲግሪ ፕሮግራም መቀጠል ያለበት ይመስላል ። እንዲሁም የኤል ኤል ኤም ሁለተኛ የሕግ ዲግሪ የሚያሰጥ ፕሮግራም ለመክፈት ማሰብ ይኖርበታል ። በሌላ በኩል ደግሞ አጫጭር በተለይ ለሕዝባዊ ድርጅቶች የፍርድ ሸንጎዎችና ለመሳሰሉት የሚዘጋጁት ፕሮግራሞች ላይ ማተኮር ይኖርበታል ። ሆኖም እነዚህ ሁሉ የሚቀጥለው የትምህርት ዘመን ጉዳዮች ናቸው ።

፯ኛ/ የወደፊቱን ሁኔታ ስንመለከት ፤

ፋኩልቲው የዛሬይቱና የነገይቱ ኢትዮጵያ የምትፈልገውን በሕግ ሙያ የሰለጠነ የሰው ኃይል የማፍራት ኃላፊነቱን ሙሉ በሙሉ ተገንዝቧል ። እንደሚታወቀው ሁሉ ትምህርት በአንድ ዓይነት ፕሮግራምም ሆነ በክፍል ትምህርት የተወሰነ አይደለም ። በፈጣን ለውጥ ላይ በሚገኝ ሕብረተሰብ ውስጥ በሕግና በፍትሕ ላይ ምርምርና ትምህርት ለማካሄድ ልዩ ትኩረት መስጠት ምንም እንኳን መንፈስን የሚቀሰቅስና የሚያረካ ቢሆንም ፤ በተግባር ለመተርጎም የዚያኑ ያህል አስቸጋሪ ነው ። የመጨረሻ ዓላማው ፍትሕ ፤ ማለትም ማኅበራዊ ፍትሕ የሆነው የኢትዮጵያ አብዮት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ ጥረቶች አርማና መሪ ኮከብ ነው ።

ፋኩልቲው ወደፊት የሚያጋጥሙትን ማናቸውንም ችግሮች እንደሚወጣና ፤ ፍትሕን ለማግኘት በሚያደርገው የወደፊት ግስጋሴና ትግል ውስጥ ተካፋይ ሆነው የሚያገለግሉ የሕግ ሰዎችን ማፍሪያ መሆኑን እንደሚቀጥል ተስፋ በማድረግ በልበ ሙሉነት ወደፊት ይመለከታል ።